ለርሱ (ለኡዱሒያ) የሚታረድ እርድ ያለው ሰው የዙልሒጃ ጨረቃ የወጣች ጊዜ ኡዱሒያውን እስኪያርድ ድረስ ከፀጉሩም ይሁን ከጥፍሩ አንዳችም እንዳይቆርጥ።

የነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሚስትና የአማኞች እናት ከሆነችው ከኡሙ ሰለማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉ: "ለርሱ (ለኡዱሒያ) የሚታረድ እርድ ያለው ሰው የዙልሒጃ ጨረቃ የወጣች ጊዜ ኡዱሒያውን እስኪያርድ ድረስ ከፀጉሩም
ይሁን ከጥፍሩ አንዳችም እንዳይቆርጥ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ኡዱሒያን ማረድ የፈለገ ሰው የዙልሒጃ ጨረቃ ግልፅ የሆነ ጊዜ ኡዱሒያውን እስኪያርድ ድረስ ከጭንቅላቱ ወይም ከብብቱ ወይም ከቀድሞ ቀመሱ ወይም ከሌላ አካሉ ላይ ያለን ፀጉርና የእጁን ወይም የእግሩን ጥፍርም እንዳይቆረጥ አዘዙ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/8954